የሰ/መ/ቁ.248155

ቀን 24/04/2016 ዓ.ም

ዳኞች ፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)
እንዳሻው አዳነ
ተሾመ ሽፈራው
ዋዚሞ ዋሲራ
ሠናይት አድነው

አመልካች ፡- በኢትዮጵያ/ወ/ቤ/ክ/መ/ኢ/ደ/ሲ/ም/ሲ//አርባ ምንጭ ሁለንቴናዊ የትምህርት ስልጠና ማዕከል - አልቀረበም

ተጠሪ ፡- አቶ ዘውዱ ዳባ - ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም የአሁኑ ተጠሪ በአመልካች ላይ በአርባ ምንጭ ከተማ የመ/ደ/ፍ/ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻነት ነው፡፡

ተጠሪ ያቀረቡት ክስም ከህዳር 09/2013 ዓ.ም ጀምሮ በአመልካች ተቋም ውስጥ የ1ኛ ደረጃ ት/ቤት ርዕሰ መምህር ሆኜ በኮንትራት ቅጥር ውል የሥራ ውሌ በሕገ ወጥ መንገድ እስከተቋረጠበት የካቲት 16/2014 ዓ.ም ሳገለግል ቆይቻለው፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች ጄጄን(JEG) ለሌሎች ሰራተኞቹ ተግባራዊ ሲያደርግ የእኔን ባለማድረጉ ቅሬታ በማቅረቤ የሁለት(2) ወር የማስጠንቀቂያ ጊዜ መስጠት ሲገባው የአንድ (1) ወር ማስጠንቀቂያ ብቻ በመስጠት የሥራ ውሌን በህገ ወጥ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ለነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

መንገድ ያቋረጠ ስለሆነና ሊከፈሉኝ የሚገቡ ክፍያዎችን በህጉ በተቀመጠው በሰባት (7) ቀናት ውስጥ ባለመክፈሉ የዘገየበት ክፍያ፣የማስጠንቀቂያ ጊዜ የ2 ወር ክፍያ፣ JEGን ተግባራዊ ባለማድረጉ ያልከፈለኝን ልዩነት ብር 3,579 .00፣የስልክና የትርፍ ሰዓት ክፍያ ከፍሎኝ ወደ ሥራ እንዲመልሰኝ ወደ ሥራ የማይመልሰኝ ከሆነ ከላይ ከተጠየቁ ክፊያዎች በተጨማሪ ከሕገ ወጥ ስንብት ጋር የተያያዙ ክፊያዎችንም ከወጪና ኪሳራ ጋር እንዲከፈለኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

አመልካች በበኩሉ በሰጠው መልስ የተጠሪ የሥራ ውሉ ለተወሰነ ጊዜ ለአንድ አመት የተደረገ በመሆኑና ጊዜው ከማብቃቱ በፊት የ1 ወር ማስጠንቀቂያ በመስጠት የነበረውን ደመወዝና ክፍያ በመፈፀም በህጋዊ መንገድ የሥራ ውሉን አቋርጠናል፡፡ ተጠሪ የመንግስት ሰራተኛ ባለመሆኑ JEG አይመለከተውም፡፡ የማስጠንቀቂያና የአንድ ወር የአመት እረፍት ክፍያውን ወስዶ ተጠቅሟል፡፡የትርፍ ሰዓት ስራ ባልሰራበት ሁኔታ ሊከፈል የሚችልበት አግባብ የለም፡፡ ስለሆነም ክሱ ውድቅ ይደረግልኝ ብሏል፡፡

ፍ/ቤቱም የአመልካች ሥራ ቀጣይነት ያለው ሆኖ ሳለ አመልካች በአዋጅ ቁ.1156/11 ቁ.10(1) ከተዘረዘሩት ውጪ የተገደበ የሥራ ውል ማድረግ የማይችል በመሆኑና የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.43160 በሥራ ውሉ ላይ ለተወሰነ ጊዜ መባሉ ብቻውን የሥራ ውሉ ለተወሰነ ጊዜ ተደርጓል የማያስብል መሆኑን አስገዳጅ ትርጉም የሰጠበት በመሆኑ በመካከላቸው የተደረገው የሥራ ውል ላልተወሰነ ጊዜ ሆኖ ሳለ አመልካች የሥራ ውሉ ጊዜው ተጠናቋል በማለት ውሉን ማቋረጡ ህገ ወጥ ተግባር ስለሆነ ተጠሪ ወዝፍ ደመወዝ ተከፍሎት ወደ ስራው ይመለስ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካችም በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለጋሞ ጎፋ ዞን ከ/ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ተጠሪ ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠረ መሆኑና ከሌላ ቦታ በጡረታ የተገለሉ መሆናቸው ባላከራከረበት ሁኔታ ላልተወሰነ ጊዜ መባል እንደማይገባው ፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.18832 ትርጉም የሰጠበት በመሆኑ የመ/ደ/ፍ/ቤቱ የሰጠው ውሳኔ አግባብ አይደለም በማለት ሽሮታል፡፡

ተጠሪ በዚህ በከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ሰበር ሰሚ ችሎቱም ምንም እንኳን በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ.18832 በጡረታ የተገለለ ሰው በድጋሜ ላልተወሰነ ጊዜ እንደማይቀጠር አስገዳጅ ውሳኔ ቢሰጥም ከአዋጅ ቁ.1156/11 ቁ.10 (1)(ሀ-ቀ) ከተዘረዘሩት ውጪ ቀጣይነት ያላቸው ስራዎችን ላልተወሰነ ጊዜ እንደተደረጉ እንደሚቆጠር ሰበር በመ/ቁ 43160 አስገዳጅ ውሳኔ የሰጠበት በመሆኑ እና በጡረታ የተገለለ ሁሉ ለተወሰነ ጊዜ ብቻ የሥራ ውል ያደርጋል ብሎ ለመደመደም የሕግ መሰረት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ለነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ስለሌለው ከፍተኛ ፍ/ቤቱ የደረሰበት ድምዳሜ አግባብነት የሌለው ነው በማለት የከፍተኛ ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመሻር የወረዳ ፍርድ ቤትን ውሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

አመልካችም ይህን የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠውን ውሳኔ ለማስለወጥ ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን አቤቱታቸውም ተጠሪ በከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ ይግባኝ ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሳያቀርቡ ለሰበር አቅርበው መዳኘቱ ከሥልጣን ውጪ ነው፡፡የአመልካችና ተጠሪ የሥራ ውል ለተወሰነ ጊዜ የተደረገ ከመሆኑም በላይ ተጠሪ ጡረታ ከወጡ በኋላ የተቀጠሩ መሆናቸው በተረጋገጠበት ሁኔታ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.18832 ከሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም በተቃረነ መልኩ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ መስጠቱ አግባብ ባለመሆኑ እንድሻር ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ተጠሪ ጡረታ ላይ በነበሩበት ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩና ጊዜው ተጠናቆ በተሰናበቱበት ሁኔታ ተጠሪ ይሰሩበት የነበረው ስራ በአዋጅ ቁ.1156/11 አንቀፅ 10 ከተዘረዘሩት የሥራ አይነቶች ውጪ በመሆኑ ላልተወሰነ ጊዜ እንደተደረገ የሚቆጠር በመሆኑ ስንብቱ ህገወጥ ነው በማለት የወሰነበትን አግባብነት በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ.18832 ከሰጠው ገዥ ተርጉም አንፃር ለመመርመር ጭብጥ ይዞ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ በሰጡት መልስ ጡረተኛ ሆንኩም አልሆንኩም የሥራ ውሉም ለተወሰነ ጊዜ ተደረገ አልተደረገ ሳይሆን ዳኝነት የጠየኩት ከህግ አግባብ ውጪ ያለ ምንም ጥፋትና ያለ በቂ ማስጠንቀቂያ የሥራ ውሌን አቋርጧል የሚል ነው፡፡አሁን እያከራከረን ላለው ጉዳይ አግባብነት ያለው የሰበር ውሳኔ የሰ/መ/ቁ.18832 ሳይሆን የሰ/መ/ቁ.43160 ነው፡፡ሥራው ቀጣይነት ያለው በመሆኑ ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ እንጂ ለተወሰነ ጊዜ የተደረገ የሥራ ውል ባለመሆኑ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ አግባብነት ያለው ነው ተብሎ እንዲፀናልኝ ብለዋል፡፡ አመልካችም አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለ መልኩ ከዚህ በላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የግራ ቀኙን አቤቱታና መልስ ለጉዳዩ ከተያዘው ጭብጥና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች አንፃር መርምረነዋል፡፡ እንደመረመርነውም ምላሽ ሊያገኝ የሚገባው አከራካሪው ነጥብ አንድ በጡረታ የተገለለ ሠራተኛ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ መሠረት እንደገና ላልተወሰነ ጊዜ የሚቀጠርበት የሕግ መሠረት ያለው መሆን አለመሆኑ ነው፡፡ በዚህ መሠረት ጉዳዩን እንደመረመርነውም የአሁን ተጠሪ ከሌላ ተቋም ውስጥ ጡረታ ከወጡ በኋላ በአመልካች ተቋም ውስጥ ለተወሰነ ጊዜ ለአንድ አመት የኮንትራት ውል ተቀጥረው በማገልገል ላይ እያሉ በሥራ ውሉ ላይ የተቀመጠው የጊዜ ገደብ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ለነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በማብቃቱ የስራ ስንብት መፈፀሙን ግራ ቀኙም ያልተካካዱትና በሥር ፍ/ቤቶች የተረጋገጠ ጉዳይ ነው። ግራ ቀኙን እያከራከረ ያለው ጉዳይ የአመልካች ስራ ቀጣይነት ያለው ከመሆኑ አንፃር እና በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 ቁ.10 ስር ከተዘረዘሩት ለተወሰነ ጊዜ ሊደረግ የሚችል ሥራዎች ውስጥ የማይመደብ በመሆኑ እና ተጠሪ ጡረታ ከወጡ በኋላ በግራ ቀኙ መካከል የተፈፀመው የሥራ ውል ቢሆንም ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ የሥራ ውል ተብሎ ከህገ ወጥ የሥራ ስንብት ጋር የተያያዙ ክፍያዎች ሊከፈሉ ይገባል ወይስ አይገባም የሚለው ነው።

በመሠረቱ የአሠሪ እና ሠራተኛ የሥራ ውል ላልተወሰነ ጊዜ ወይም ለተወሰነ ጊዜ ወይም ለተወሰነ ሥራ የሚደረግ ስለመሆኑ የአዋጅ ቁ.1156/2011 አንቀጽ 9 እና 10 ያስገነዝቡናል።

በእድሜ ምክንያት በጡረታ የተገለለ ሰው ተመልሶ ላልተወሰነ ጊዜ የሚቀጠር መሆን አለመሆኑን በተመለከተ በአዋጁ በግልጽ የተደነገገ ባይሆነም ከጡረታ ዕላማ አንጻር መመልከት አስፈላጊ ይሆናል።

ተጠሪ በአመልካች ት/ቤት የተቀጠሩት እድሜያቸው ለጡረታ በመድረሱ ከሌላ ተቋም በጡረታ ከተገለሉ በኋላ መሆኑን ከመዝገቡ ተረድተናል። ጡረታ አንድ ሠራተኛ እድሜውን ሙሉ ብቃት ያለው ሠራተኛ ሆኖ እንደማይቀጥል ከእድሜው መግፋት ጋር የሥራ ውጤታማነቱ እንደሚቀንስ ስለሚታመን እድሜውን ሙሉ በተቀጠረበት ሥራ ላይ እንዲቀጥል መደረጉ የአሰሪውን ጥቅም ይጎዳል ተብሎ ስለሚታመን ሠራተኛው ከሥራ ተሰናብቶ አሰሪው ብቃት ያለውን ሠራተኛ በቦታው አንዲተካ ለማስቻል ሠራተኛው በጡረታ የሚገለልበት ስርዓት ነው። ተጠሪ በዚህ መልኩ የጡረታ እድሜያቸው ደርሶ በጡረታ የተገለሉ ናቸው። ምንም እንኳን በጡረታ የተገለለ ሰው ሥራ መስራት አይችልም የሚባል ባይሆንም አንድ አሰሪ በጡረታ የተገለለውን ሠራተኛ በድጋሚ ላልተወሰነ ጊዜ ቀጥሮ ያሰራል ለማለት አይቻልም።

እንግዲህ ከላይ እንደተገለጸው በጡረታ የተገለለ ሰው እንደገና ላልተወሰነ ጊዜ የሚቀጠርበት ሁኔታ በአዋጁ በግልጽ የተደነገገ ባለመሆኑ በፌደራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 18832 በጡረታ የተገለለ ሰው አንደገና ላልተወሰነ ጊዜ የስራ ውል መፈጸም እንደማይችል የሕግ ትርጉም ተሰጥቶበታል።

ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሚሰጠዉ የህግ ትርጉም ተፈጻሚነቱን በተመለከተ ዉሳኔዉ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በማንኛዉም ደረጃ ለሚገኝ የፌደራል ወይም የክልል ፍርድ ቤት አስገዳጅ እንደሆነ በፌደራል ፍርድ ቤቶች በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2 (4) (ሸ) እና) አንቀጽ 26 (3) ተደንግጓል።

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ለነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ከአዋጁ ድንጋጌ ሲታይ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ.18832 በጡረታ የተገለለ ሰው በድጋሜ ላልተወሰነ ጊዜ እንደማይቀጠር በአስገዳጅነት የተሰጠውን የሕግ ትርጉም ከተቀበለ በኋላ በአዋጅ ቁ.1156/11 አንቀጽ 10 (1) (ሀ-ቀ) ከተዘረዘሩት ውጪ ስለሆነ የሥራ ውል ላልተወሰነ ጊዜ ስለሚሆን ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ማለት ተጠሪ ወደ ሥራ እንዲመለስ የወረዳ ፍርድ ቤትን ውሳኔ በማጽናት መወሰኑ ሕጉን መሠረት ያላደረገ መሆኑን ያስገነዝበናል፡፡

በሌላ በኩል የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በቅፅ 9 የመ/ቁ. 43160 ላይ የሰጠው የህግ ትርጉምም ከጡረታ በኋላ ድጋሜ ስለሚደረግ የሥራ ውል ሳይሆን ከጡረታ በፊት ያለውን ጉዳይ የሚመለከት በመሆኑ አሁን ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት ያለው የህግ ትርጓሜ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በአጠቃላይ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ከላይ እንደተመለከተው ሕጉንና የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም በመቃረን የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ውሳኔ

1. የደ/ብ/ብ/ሕ/ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትበመ/ቁ.41924 ግንቦት 09 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የአርባ ምንጭ ከተማ መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ.35096 ጳጉሜ 02 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የጋሞ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 45415 ህዳር 02 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.348 (1) መሰረት ፀንቷል፡፡
3. በዚህ መዝገብ ሐምሌ 05 ቀን 2015 ዓ.ም የተሰጠው እግድ ተነስቷል፡፡ይፃፍ፡፡
4. በዚህ ክርክር ግራ ቀኙ ያወጡትን ወጪ ለየግላቸው ይቻሉ፡፡
5.

ትዕዛዝ

1. የውሳኔ ግልባጭ ለግራ ቀኙ ይሰጣቸው፡፡
2. መዝገቡን ዘግተን ወደ መዝገብ ቤት መልሰናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ለነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ፅ/ወ